# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

አቅራቢዎች



## የተዋበችው ንግስት አስቴር፡፡

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest, Alastair Paterson

ያሻሻለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2022 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

በአንድ ዘመን አስቴር የተባለች የተዋበች ሴት ነበረች፡፡ እናቷና አባቷ ሲሞቱ ፣ የአስቴር አጎት ልጅ የሆነው መርደኪዮስ አሳደገት፡፡ አስቴርም እንደ መልካም ሴት ልጅ ሆና የአጎቷ ልጅ የሆነውን መርደኪዮስን በመታዘዝ ታከበረው ነበረ፡፡





አስቴር በፋርስ ኖራለች። ነገር ግን ፣ አስቴር ፋርሳዊ አልነበረችም ፤ አይሁዳዊት ነበረች። የእርሷ የቀደሙ አያቶቿ ወደ ፋርስ የመጡት በጦርነት ምርኮኞች በመሆን ነበረ።
በአስቴር ዘመን ፣ ብዙ አይሁዳዊያን በፋርስ ይኖሩ ነበረ።

የፋርስ ንጉስም ከሁሉም ሃገራት
ለመጡ ንግስቶች የእራት ግብዣ
አሰናድቶ ነበረ፡፡



ወንዶቹም ከአስጢንጋ
አብረው ለግብዣ
ተሰናድተው ከነበሩ
ንግስቶች ተለይተው
ይመገኑ ነበረ፡፡
የሰከረው ንጉስም
ንግስት አስጢን
የንጉሶችን ዘውድ ደፍታ
ውበቷን እንድታሳያቸው
ትዕዛዝ አወጣ፡፡ ንግስት
አስጢን ግን
አልተቀበለችውም፡፡

ሴቶች ባሎቻቸውን ማክበር
እንዳለባቸው ለማሳየት ፣ ንጉሱ
የአስጢንን ዘውድ እንዲወሰድ
የሚያዝ ሕግ አወጣ፡፡ ከዚያም
በኋላ ንግስት አትሆንም፡፡



የአዲስ ንግስት ፍለጋም ተጀመረ፡፡ በአገዛዙ ሁሉ ውስጥ ካሉ ቆነጃጅት ፣ ንጉሱ ሚስቱ እንድትሆን በሚል አስቴርን መረጣት፡፡ የንግስናውን ዘውድ በእርሷ ራስ ላይ አደረገው፡፡ የአጎቷ ልጅ እንዳታደርገው ከልክሏታልና ፣አስቴረም አይሁዳዊ መሆንዋን ለንጉሱ አልነገረችውም ነበረ፡፡





የአስቴርንም ወሬ ለመስማት
እንዲመቻቸው የአጎቷ ልጅ መርዶክዮስ
በቤተመንግስቱ ደጃፍ ላይ ተቀምጦ
ነበረ፡፡ አንድ ቀን ሁለት
የቤተመንግስቱ አገልጋዮች ንጉሱን
ለመግደል እቅድ ሲያወጡ
ይሰማቸዋል፡፡ መርኮክዮስም የንጉሰን
ሕይወት ሊያተርፍ የሚችል
ማስጠንቀቂያ ወደ ቤተመንግስቱ ላከ፡፡
አገልጋዮቹም ታሰሩ ፤ መርኮክዮስ ግን
የንጉሱ መዝገብ ላይ ስሙ ሰፈረ፡፡

ከንጉሱ በመቀጠል ሁለተኛው አዛዥ ሰው ሀማ ይባል ነበረ፡፡ ሐማ ሲያልፍ ሁሉ ሰው ይሰግድ ነበረ፡፡ ከአንድ ሰው በስተቀር ፤ ሁሉም! እንደ አይሁዳዊ ፣ መርዶክዮስ ሕያው አምላክን ያመልክ ነበረ፡፡



ሐማ መርዶክዮስን እጅግ ይጠላው ነበረ ፤ በዚያም
ምክንያት እርሱንና በፋርስ ያሉ አይሁዳዊያንን ሁሉ
ሊገድላቸው ወስኖ ነበረ። እንዴት አስፈሪ ነገር ነው!
እጅግ ክፉ የሆነው ሐማም ንጉሱ በፋርስ
ያሉ አይሁዳዊያን ሁሉ እንዲገደሉ
የሚያዝ ሕግ እንዲወጣ ሸነገለው።





ይሄ እጅግ ከፉ ሕግ ነው፡፡
አይሁዳዊያንና ፋርሳዊያን ሁሉ
አለቀሱ፡፡ ነገር ግን አስታውስ ፤
እግዚአብሔር አስቴርን ንግስት
እድርጓት ነበረ ፤ እርሷም
አይሁዳዊ ሴት ነበረች፡፡
ይሐንን ሚስጥሯን ከንጉሱ
ትጠብቀ ይሆን; ወይስ ፤
የራሷን ሕዝብ ለማዳን ስትል
ራሷን ልታስገድል ትችላለች?

እግዚአብሔር ለአስቴር እጅግ አስደናቂ ሐሳብን ሰጣት፡፡ ንጉሱንና ሐማን ወደ እራት ግብዣው ጠራቻቸው፡፡ ንጉሱም የጠየቀችውን ነገር ሁሉ እንደሚያደርግላት ቃል ገባላት፡፡ አስቴርም "ንጉሱና ሐማ ወደ እራት ግብዣው እንዲመጡላት ጠየቀች፡፡" ከዚያም ምን እንደምትፈልግ ለንጉሱ ትነግረዋለች፡፡



በመሐከል ፣ ሐማ መርዶኪዮስ
የሚታሰርበትን ትልቅ እንጨት አዘጋጀ።



በዚያም ምሽት ንጉሱ ፈጽሞ አልተኛም ነበረ። የቤተመንግስቱን መዝገብ ሲያገላብጥ መርዶክዮስ ላደረገው መልካም ነገር ሽልማት አልተሰጠውም ነበረ። በሚቀጥለውም ማለዳ ፣ ንጉሱ ሐማን ጠየቀው። “ንጉስ ለወደደው ምን ይደረግለታል;" ሐማም አጅግ ደስ አለው። እርሱ ያሰበው ንጉሱ አውቆ እንደተናገረ ነበረ።



ሐማም መርዶክዮስ እንዲሰቀል የንጉሱን ትዕዛዝ ይጠይቅ ነበረ፡፡ እንጨቱ ተዘጋጅቶ ነበረ፡፡ አሁንም ያ ጥያቄ ይጠበቅ ነበረ፡፡ ሐማም ደስታን ተሞልቶ ፣ “ያ ሰው የንጉሱን ልብስና ዘውድ ይልበስ፡፡” አለ፡፡ “በንጉሱ ፈረስ ላይ አስቀምጡት ፤ ሰው ሁሉ እንዲያየውም የንጉሱ ልኡል እየመራው በከተማ መካከል እነዲያልፍ አድርጉት፡፡” ብሎ ተናገረ፡፡ ንጉሱም ፣ “ፍጠኑና ይህንን ነገር ለመርዶክዮስ አድርጉለት፡፡” አላቸው፡፡



ሐማ መርዶክዮስ እንዲከብር በከተማው መካከል ይዞት ሲዞር ምን እየተሰማው ይመስላችኋል; ከቀድሞው በላይ መርዶክዮስን ጠልቶት ነበረ። ሐማ “ትንሽ ጠብቁ!” ሳይል አይቀርም ፤ “ከሁሉም አይሁዳዊያንጋ በቅርቡ ይሞታል።”



ከዚያ ቀንም በኋላ፣ ሐማና ንጉሱ በንግስቲቱ የእራት ግብዣ ላይ ተገኙ፡፡ "የአንተ ቅሬታ ምንድነው፡፡" ብሎ ንጉሱ ጠየቀው፡፡ የገባውን ቃል ኪዳን ንጉሱ አልረሳውም ነበረ፡፡ ወደ ሐማ እየጠቆመ ፣ ንግስት አስቴርም የሐማን ክፉ ሴራዎች ሁሉ ለንጉሱ ነገረችው፡፡ ንጉሱም "ስቀሉት!" አለ፡፡



ከዚያም ንጉሱ አይሁዳዊያን ራሳቸውን እንዲከላከሉ የሚል ሌላ ሕግ አወጣ፡፡ ሁሉም ዳኑ! በንጉሱም ትዕዛዝ መርዶክዮስ ከንጉሱ ሁለተኛ ሆኖ ተሾመ ፤ አይሁዳዊያን በመደሰት እርስበርሳቸው ስጦታን ተሰጣጡ፡፡ ዛሬም ድረስ አይሁዳዊያን በንግስት አስቴር አማካይነት የዳኑበትን ቀን ያስቡታል፡፡



የተዋበችው ንግስት አስቴር።

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

አስቴር

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

# መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን
እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል።
የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን
አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው።
ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ!
ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል
ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤
እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት
ለመሞት ሰትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ
ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን
ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና
እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16